# የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) በወላይታ ዞን የተካሄደውን የድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን አስመልክቶ የሰጠው የመጀመሪያ ደረጃ የትዝብት ሪፖርት

**ሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

## ሀ) መግቢያ

***የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ)*** ከ175 በላይ ሀገር በቀል የሲቪል ማህበራትን ያቀፈ ህብረት ነው። ኅብረቱ ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ የዜጎች የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ሲሆን ዋና ዓላማውም  በኢትዮጵያ ውስጥ አካታች፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለው ምርጫ እውን እንዲሆን  አስተዋጽዖ ማድረግ ነው።

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ የሚገኙ ከ10 የሚበልጡ ዞኖች ከ2012 ዓ.ም. ጀምሮ የራሳቸውን ክልላዊ መንግሥት ለመመስረት ጥያቄ ማቅረባቸው ይታወቃል።[1] በዚህም መሰረት በሕዳር 2011 ዓ.ም እና በመስከረም 2014 ዓ.ም ከተካሄዱ የሕዝበ ውሳኔዎች በኋላ የሲዳማ ክልል እና የደቡብ ምዕራብ ክልሎች ተመስርተዋል።

በተመሳሳይ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙ ስድስት ዞኖችና አምስት ልዩ ወረዳዎች አዲስ ክልል እንዲመሰረት በየምክር ቤቶቻቸው አማካኝነት ውሳኔ አሳልፈዋል። በዚህም መሰረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስማቸው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዞኖች እና ልዩ ወረዳዎች ሕዝበ-ውሳኔ እንዲያደራጅ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያ ሰጥቷል። የምርጫ ቦርድም ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም. በስድስቱ ዞኖች (ኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዴኦ እና ጎፋ) እና በደቡብ ክልል አምስት ልዩ ወረዳዎች (ቡርጂ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ አማሮ እና ደራሼ) ሕዝበ ውሳኔ ማካሄዱ ይታወሳል። ኅብረት ለምርጫም በስድስቱ ዞኖችና በአምስቱ ልዩ ወረዳዎች 434 ተቀማጭ እና 76 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን መልምሎ በማሰልጠን ለትዝብት አሰማርቷል። ነገርግን የምርጫ ቦርድ በመራጮች ምዝገባ እና በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ከፍተኛ የሆነ የህግ ጥሰት መፈፀሙን በመጥቀስ በወላይታ ዞን የተካሄደውን ሕዝበ ውሳኔ ውጤት ሰርዟል። ይህንንም ተከትሎ የምርጫ ቦርድ በወላይታ ዞን ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም. የሕዝበ ውሳኔው በድጋሚ እንደሚካሄድ ለባለድርሻ አካላት አስታውቋል። በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ ለወላይታ ዞን አዋሳኝ በሆኑ ዞኖች የሚገኙ ስድስት አባል ድርጅቶቹን[2] በማሳተፍ 190 ታዛቢዎችን መልምሎ፤ ከመካከላቸው በአጠቃላይ 146 (118 ተቀማጭ እና 28 ተንቀሳቃሽ) ታዛቢዎችን አሰማርቶ የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን በመታዘብ  ይህንን የመጀመሪያ ደረጃ የትዝብት ሪፖርት አዘጋጅቷል።

ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት የተዘጋጀው የድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ሂደቱን በ117 የምርጫ ጣቢያዎች ከታዘቡ ከ117 ተቀማጭ ታዛቢዎች የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ነው። በተጨማሪም ኅብረት ለምርጫ ካሰማራቸው 28 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ያሰባሰባቸውን የአሳሳቢ ኹነት መረጃዎች በዚህ ሪፖርት ውስጥ አካቷል። ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈፃሚዎች ወደ ምርጫ ጣቢያ መድረሳቸውን፣ የምርጫ ጣቢያዎችን አዘገጃጀት እና አከፋፈት፣ የመራጮችን ምዝገባ፣ ድምጽ መስጠት፣ የምርጫ ጣቢያ መዘጋት፣ የድምፅ ቆጠራ እና የውጤት ማጠቃለያ ላይ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ይዟል።

## ለ) ዋና ዋና ግኝቶች

ኅብረት ለምርጫ በወላይታ ዞን በድጋሚ የተካሄደውን ሕዝበ ውሳኔ የመታዘቡ ዋና ዓላማ በሂደቱ ላይ ሲስተማቲክ (systematic) እና ተጨባጭ የሆኑ መረጃዎችን በማስባሰብ ግልፅነት እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የበኩሉን አስተዋፅዖ ማበርከት ነው። ከዚህ አንጻር ኅብረቱ ያሰማራቸው ተቀማጭ ታዛቢዎች በየተመደቡበት የምርጫ ጣቢያ ከማለዳው 11:30 በመገኘት ሁሉንም የድምፅ አሰጣጥ ሂደቶች ጊዜያዊ የሕዝበ ውሳኔ ውጤት መለጠፍን ጨምሮ ሂደቱን በመታዘብ ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን፤

---

[1] Policy Research Institute, Grassroots Approach to Understanding the Growing Demand for Statehood In SNNPR, Ethiopia (A Short Research Report), October 1, 2020, p. 8

[2] እነዚህም የአባል ድርጅቶች፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ መምህራን ማህበር፣ ሻይኒ ዴይስ፣ ሪሰሬክሽን ላይፍ ኤንድ ዴቨሎፐመንት ኦርጋናይዜሽን፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ኅብረት፣ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌደሬሽን እና የሀዲያ ወጣቶች ማህበር ናቸው።

ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች በበኩላቸው በበርካታ የምርጫ ጣቢያዎች በመዘዋወር የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን በመታዘብ እንዲሁም አሳሳቢ ኹነቶች ሲከሰቱ ለኅብረት ለምርጫ ወዲያውኑ ሪፖርት አድርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ የሚከተሉት ዋና ዋና የትዝብት ግኝቶች ቀርበዋል፡-

***ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስን በተመለከተ***

1. የምርጫ አስፈፃሚዎች ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ የምርጫ ጣቢያዎች ለድምጽ መስጠት ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከመክፈቻ ሰአቱ በፊት ወደ ምርጫ ጣቢያ መድረስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የኅብረቱ ታዛቢዎች ከጠዋቱ 11:30 ላይ በየተመደቡባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ሲደርሱ 97በመቶ በሚሆኑት ጣቢያዎች በአማካኝ 5 የምርጫ አስፈፃሚዎችን መኖራቸውን ታዝበዋል፤
2. ኅብረት ለምርጫ በታዘበባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም ኅብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች እንዲገቡ እና እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል፤

***የምርጫ ጣቢያዎች አከፋፈት***

3. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎች ከማለዳው 12 ሰአት ጀምሮ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ የተጀመረው ከማለዳው 12 ሰአት እስከ 1፡00 ሰዓት ድረስ ነበር፤
4. የምርጫ ህጉ እንደ ወታደራዊ ካምፖች፣ የግል መኖሪያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሀይማኖት ተቋማት ቅጥር ውስጥ፣ በጤና ተቋማት፣ በመዝናኛ ማዕከላት እና የፖለቲካ ፓርቲ ጽህፈት ቤቶች ባሉ ቦታዎች የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም ይከለከላል፡፡ በዚህም መሰረት ኅብረቱ ከታዘባቸው ጣቢያዎች መካከል 98 በመቶ የሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ህጉ ባልተከለከሉ ቦታዎች መቋቋማቸውን፤ ነገር ግን ***በአፋ ወረዳ ገሱባ -1 ቀበሌ 07 አንድ የምርጫ ጣቢያ*** የምርጫ ህጉ ከደነገገው በተቃራኒ በጤና ጣቢያ ውስጥ መቋቋሙን መታዘብ ተችሏል፤
5. የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ የምርጫ ህጉ በድምጽ መስጫ ቀን ከምርጫ ጣቢያዎች በ200 ሜትር ርቀት ውስጥ ምንም አይነት የምርጫ ቅስቀሳ ማድረግን በግልፅ ይከለክላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በድምጽ መስጫ ቀን ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ውስጥ ምንም አይነት ቅስቀሳ አለመደረጉን የኅብረቱ የታዛቢዎች ሪፖርት ያመለክታል፤

***የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት***

6. ኅብረቱ የታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙበትን ቦታ በተመለከተ 23 በመቶው በከተሞች ፣ 8 በመቶው በከፊል ከተሞች እና ቀሪው 69 በመቶው ደግሞ በገጠር አካባቢ የተቋቋሙ መሆናቸውን ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል፤
7. ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሃይ የሚያስጠልሉ ዳሶች መኖር በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ከተሰማሩባቸው 33 በመቶዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች ነበሯቸው፤
8. የምርጫ ጣቢያዎችን በተገቢው መንገድ ተቋቁመዋል ለማለት የድምጽ መስጫ ቁሳቁሶች መሟላት አለባቸው፡፡ ኅብረት ለምርጫ ያሰማራቸውን ታዛቢዎች አስፈላጊ የሆኑ እንደ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ ሕጋዊ የቦርዱ ማህተም፣ የውጤት ማመሳከሪያ ቅጽ፣ የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን ማሸጊያ እንዲሁም የቅሬታ መቀበያ ቅጾች፣ የድምጽ መስጫ ቁሳቁሶች መሟላታቸውን እንዲያረጋግጡ ተጠይቀው ነበር፡፡ በዚህም መሰረት የቅሬታ መቀበያ ቅጾች ካልተሟሉባቸው 2 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች በስተቀር በሁሉም ጣቢያዎች የምርጫ ቁሳቁሶች ተሟልተው ነበር፤
9. ትዝብት በተደረገባቸው በሁሉም ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ከመጀመራቸው በፊት የመራጮች መዝገቦች ባዶ መሆናቸውን አሳይተው ነበር፤
10. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ከመጀመራቸው አስቀድሞ የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ትዝብት በተደረገባቸው በሁሉም ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ከመጀመራቸው በፊት የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን አሳይተው ነበር፤

11. የምርጫ ሕጉ በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ቢያንስ ሶስት አስፈፃሚዎች መገኘት እንዳለባቸው ያስቀምጣል። ነገርግን በወላይታ ዞን በተደረገው የድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ጣቢያ መገኘት ያለባቸው ዝቅተኛ የአስፈፃሚዎች ቁጥር ከሶስት ወደ አምስት ከፍ ተደርጓል። ምንም እንኳን ቦርዱ ይህንን መመሪያ ቢያስተላልፍም በሶዶ ዙሪያ በሚገኙ ሶስት የምርጫ ጣቢያዎች ከቦርዱ መመሪያ ውጭ ሶስት የምርጫ አስፈፃሚዎች ብቻ ተገኝተው ነበር። እነዚህ የምርጫ ጣቢያዎችም ***ሁምቦ ላሬና የምርጫ ጣቢያ ሁምቦ ላሬና 3፣ የቁራ ምርጫ ጣቢያ - 1 እና ዌሺ ጋሌ የምርጫ ጣቢያ ዌሺ ጋሌ 'ለ' ናቸው፤***

12. የምርጫ ሕጉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በምርጫ ጣቢያዎች ያቋቁማል። በዚህም መሰረት ኅብረቱ ከታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ20 በመቶዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የተቋቋሙ ቢሆንም፤ በ80 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አልተቋቋሙም፤

13. ኅብረቱ ከታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 8 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በኅብረት ለምርጫ ከተሰማሩ ታዛቢዎች ውጪ ሌሎች ታዛቢዎች የተገኙ ሲሆን፤ 92 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በኅብረት ለምርጫ የተሰማሩ ታዛቢዎች ብቻ ተገኝተው ነበር፤

**በሕዝበ ውሳኔው ሂደት የሴቶች ተሳትፎን በተመለከተ**

14. ኅብረት ለምርጫ በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በአማካኝ 5 የምርጫ አስፈፃሚዎች የተገኙ ሲሆን ከእነዚህ መካከል በአማካይ 2ቱ ሴቶች ነበሩ፤

15. ኅብረቱ ታዛቢዎቹን ካሰማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 31 በመቶ የሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ኃላፊዎች ሴቶች ነበሩ። በተለየ ሁኔታ **በሶዶ ከተማ ቁራ ቀበሌ የምርጫ ጣቢያ 09** ሁሉም የምርጫ አስፈጻሚዎች ሴቶች ሆነው ተስተውለዋል፤

16. ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከነበሩ የጸጥታ ሃይሎች መካከል 30 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ነበሩ።

**ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ ለሚያጠቡ እናቶች እና እርጉዝ ሴቶች የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት**

17. ከምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት አንጻር ሌላው ወሳኝ ጉዳይ እንደ አረጋውያን፣ ህጻናትን የያዙ እና አካል ጉዳተኞችን እና መሰል የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት ነው። ከዚህ አኳያ ኅብረቱ ከታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 90 በመቶ የሚሆኑት ከላይ ለተጠቀሱት መራጮች ተደራሽ ሲሆኑ፣10 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች ግን ተደራሽ አልነበሩም፤

18. ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኅብረቱ ታዛቢዎች የተመለከቱት ሌላው ጉዳይ የምርጫ ጣቢያዎች ለሁለቱም ጾታዎች (ወንድ እና ሴት) ያላቸውን ተደራሽነት የሚመለከት ሲሆን ኅብረቱ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 99 በመቶ የሚሆኑት ለወንድ እና ለሴት መራጮች ተደራሽ እንደነበሩ ያመለክታል፤

## ሐ) የመራጮች ምዝገባና ድምጽ አሰጣጥ ሂደት

19. ሁሉም የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ጣቢያዎች በመራጮች ምዝገባ እና በድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ወቅት ከጣቢያው ለቀው እንዲወጡ አልተጠየቁም፤

20. የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው 99በመቶ በሚሆኑት ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ አቅመ ደካሞች፣ ነፍሰጡር ሴቶች እና ህጻናት ልጆች ለያዙ ወላጆች ቅድሚያ እንዲሰጥ አድርገዋል፤

21. ትዝብት ከተደረገባቸው 92 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች አካል ጉዳተኞች በመረጡት የግል ረዳት እገዛ እንዲያገኙ ተፈቅዶላቸዋል። በሌላ በኩል 8 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ምንም የተለየ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው መራጮች እንዳልታዘቡ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል፤

22. የምርጫ ህጉ መራጮች ለመመዝገብ እና ድምጽ ለመስጠት የነዋሪነት ወይም የማንነት ማረጋገጫ ማሳየት እንዳለባቸው ይደነግጋል። በመሆኑም ነዋሪነታቸውን ወይም ማንነታቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ለማቅረብ የማይችሉ ወይም

ነዋሪነታቸውን በምስክሮች ማረጋገጥ የማይችሉ መራጮች በምዝገባና በድምጽ አሰጣጥ ሂደት መሳተፍ አይችሉም። በዚህም መሰረት ኅብረቱ ታዛቢዎቹን ካሰማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል፦

- 35 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 የሚሆኑ መራጮች ማንነታቸውን ወይም መኖሪያ አድራሻቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው እንዲመዘገቡ እና ድምጽ እንዲሰጡ አልተፈቀደላቸውም፤

- ታዛቢዎቹ ከነበሯቸው 6 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ከ11 አስከ 20 የሚሆኑ መራጮች የማንነት ወይም የነዋሪነት ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው እንዲመዘገቡ እና ድምጽ እንዲሰጡ አልተፈቀደላቸውም፤

23. የምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደት እየተከናወነ ባለበት ወቅት ከሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም አንስቶ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የተሰጡ የቀበሌ መታወቂያ ካርዶችን ይዘው የሚመጡ ዜጎችን እንዳይመዘገቡ እና እንዳያስመርጡ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለምርጫ አስፈፃሚዎቹ መመሪያ ሰጥቶ ነበር። በተጨማሪም ቦርዱ ምንም እንኳን የቀበሌ መታወቂያ ካርድ ቢኖራቸውም እድሜያቸው ለመምረጥ ያልደረሱ የሚመስሉ መራጮች እንዳይመዘግቡም ከልክሏል።

    - 13 በመቶ በሚሆኑት የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 የሚደርሱ መራጮች የማንነት ወይም የመኖሪያ ማረጋገጫ ሰነዶችን ቢያቀርቡም እንዲመዘገቡ እና እንዲመርጡ አልተፈቀደላቸውም፤
    - 1 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከ11 እስከ 20 የሚሆኑ መራጮች የማንነት ወይም የመኖሪያ ቦታ ማረጋገጫ ቢያቀርቡም መመዝገብ እና መምረጥ አልቻሉም፤
    - በተመሳሳይ መልኩ 1 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከ20 በላይ መራጮች የማንነት ወይም የመኖሪያ ቦታ ማረጋገጫ ቢያቀርቡም መመዝገብ እና መምረጥ አልቻሉም፤

24. የምርጫ ህጉ መራጮች ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት በጣታቸው ላይ የማይጠፋ ቀለም እንዲቀባ ያዛል። በዚህ መሰረት ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች 98 በመቶ በሚሆኑት የማይጠፋ ቀለም በአግባቡ በመራጮች ጣት ላይ የተደረገ ሲሆን፤ ትዝብት ከተደረገባቸው ጣቢያዎች 2 በመቶ በሚሆኑት ከ1 እስከ 10 በሚሆኑ መራጮች ጣት ላይ የማይጠፋ ቀለም አልተቀባም፤

25. የምርጫ ቦርድ በዚህ የድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ በተመሳሳይ ቀን እንዲካሄድ በማድረጉ በሁሉም የህብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በታዘቡባቸው ጣቢያዎች ማንም መራጭ ሳይመዘግብ እንዲመርጥ አልተፈቀደለትም፤

26. የምርጫ ሕጉ የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች ሁሉንም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ለመራጮች ከመስጠታቸው በፊት ማህተም እንዲያደርጉባቸው ይደነግጋል። በአንድ አጋጣሚ ብቻ (***በሶዶ ከተማ ቶሜ ገራራ ምርጫ ጣቢያ 4***) አንድ መራጭ ማህተም ያልተደረገበት የድምጽ መስጫ ወረቀት ተቀብሎ ድምጽ ሰጥቷል። ነገርግን የምርጫ አስፈጻሚዎች ከህጉ በተጻረረ መልኩ በድምፅ ቆጠራ ወቅት በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ ማህተም በማድረግ እንዲቆጠር አድርገዋል፤

27. የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ምስጢራዊነት በተመለከተ ትዝብት ከተደረገባቸው 98 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ቀኑን ሙሉ ምስጢራዊነቱ ተጠብቆ ነበረ፤

28. ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎቹን በማሰማራት በታዘባቸው ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ግልጽ በሆነ ቦታ ላይ ተቀምጠው ይታዩ ነበር፤

29. በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች መገኘትን በተመለከተ 1 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ እየተከናወነ በነበረበት ጊዜ ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተገኝተው ነበር። እነዚህ ጥሰቶች በዚህ ሪፖርት የአሳሳቢ ሁነት ክፍል ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል፤

30. በዕለቱ ትዝብት ከተደረገባቸው ጣቢያዎች መካከል 1 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ለተወሰነ ጊዜ ተቋርጦ ነበር። ለዚህም ምክንያት የነበረው የምርጫ ቦርድ ካለፉት ስድስት ወራት ወደዚህ አዲስ መታወቂያ ካርድ የወሰዱ ነዋሪዎች እንዳይመዘገቡ ለምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ባስተላለፈው መመሪያ ምክንያት ነው፤

31. በአንድ የምርጫ ጣቢያ (1 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች) የማስፈራራት እና የማዋከብ ድርጊቶች እንደነበሩ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። እነዚህ ጥሰቶች በዚህ ሪፖርት የአሳሳቢ ሁነት ክፍል ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል፤

32. ኅብረት ለምርጫ በሕዝበ ውሳኔው የድምጽ አሰጣጥ ሂደት ወቅት ተሳታፊ በነበሩ ሴት መራጮች፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች እና ታዛቢዎች ላይ የማስፈራራት እና የማዋከብ ተግባራት ስለመፈፀማቸው ምንም አይነት ሪፖርት አልደረሰውም፤

33. 82 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች እየተከናወኑ በነበሩበት ሰዓታት በሙሉ የጸጥታ አካላት ከምርጫ ጣቢያው ውጭ ተገኝተው ነበር። ይሁን እንጂ 9 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ውጭ የጸጥታ አካላት ለተወሰኑ ሰዓታት የተገኙ ሲሆን፤ በቀሪዎቹ 9 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ውጭ ላይ ግን ምንም አይነት የጸጥታ አካላት አልነበሩም፤

34. የምርጫ ህጉ በሚያዘው መሰረት የሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የመዝጊያ ሰዓት ከምሽቱ 12 ሰዓት የነበረ ቢሆንም በዕለቱ ቦርዱ የድምጽ መስጠት ሂደቱን እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ድረስ እንዲራዘም አድርጓል። በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 7.7 በመቶ የሚሆኑት ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት በፊት የተዘጉ ሲሆን፤ 71.8 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከምሽቱ 12፡00 እስከ 1፡00 ሰአት ባለው ጊዜ ተዘግተዋል። ቀሪዎቹ 20.5 በመቶ የሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ከምሽቱ 1፡00 በኋላ ተዘግተዋል፤

35. ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች 39 በመቶ በሚሆኑት ምርጫ ቦርድ ባስቀመጠው መዝጊያ ሰዓት (ከምሽቱ 1፡00 ሰአት) ድረስ ድምጽ ለመስጠት ሰልፍ ላይ የነበሩ መራጮች ድምጽ እንዲሰጡ የተፈቀደላቸው ሲሆን በቀሪዎቹ 61 በመቶ በሚሆኑት ጣቢያዎች ላይ በመዝጊያ ሰአት ላይ ምንም አይነት የድምጽ ሰጪዎች ሰልፍ አልነበሩም፤

## መ) የድምፅ ቆጠራ

36. ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎቹን ባሰማራባቸው ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት ታዛቢዎቹ ከምርጫ ጣቢያው ለቀው እንዲወጡ አልተጠየቁም፤

37. የምርጫ ህጉ የድምጽ ቆጠራ በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል። በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎቹን ባሰማራባቸው ሁሉም ጣቢያዎች ላይ ቆጠራ የተካሄደው በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ነበር፤

38. የኅብረቱ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የቆጠራው ሂደት የተቋረጠበት ሁኔታ አልተስተዋለም፤

39. 1 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በቆጠራው ሂደት ወቅት ጣልቃ ገብነት፣ ወከባ እና/ወይም ማስፈራራት እንደነበር ሪፖርት ተደርጓል። ይህም በአሳሳቢ ኹነት ክፍል በዝርዝር ተካቷል፤

40. ትዝብት በተደረገባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያው ኃላፊዎች በድምፅ ቆጠራው ወቅት ሁሉንም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በግልፅ አሳይተዋል፤

41. የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የጣቢያዎቹ ኃላፊዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ዋጋ ያላቸው መሆን እና አለመሆናቸውን ለመወሰን ወጥነት ያላቸውን መመዘኛዎችን በቋሚነት ተጠቅመዋል።

42. ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 96 በመቶ በሚሆኑት የማመሳከሪያ እና የውጤት ቅጽ ቅጂዎች ከምርጫ ጣቢያው ውጪ ተለጥፈው ነበር። በአንፃሩ 4 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች የማመሳከሪያ እና የውጤት ቅጽ ቅጂዎች ከምርጫ ጣቢያው ውጪ አለመለጠፋቸውን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን፤ እነዚህም ምርጫ ጣቢያዎች ***ጊዶ ምርጫ ጣቢያ 02፣ ጣዲሳ ምርጫ ጣቢያ 05፣ ኮዶ ምርጫ ጣቢያ ኮዶ፣ ጊዶ ምርጫ ጣቢያ 01፣*** እና ***ዋርቢራ ሱቄ ምርጫ ጣቢያ ሱኬ 'ለ'2*** ናቸው።

## ሠ) አሳሳቢ ኹነቶች

አሳሳቢ ኹነቶች በጠቅላላ የሕዝበ ውሳኔ ሂደቶች እንዲሁም ውጤት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ከምርጫ ሕጉ ያፈነገጡ ከባድ የአሰራር ግድፈቶች ናቸው። በመሆኑም ኅብረት ለምርጫ እነዚህ አሳሳቢ ሁነቶች በሚከሰቱበት ወቅት ሁሉም ታዛቢዎች በአፋጣኝ ወደ መረጃ ማዕከሉ ሪፖርት እንዲያደርጉ መመሪያ አስተላልፏል። በዚህም መሰረት የኅብረት ለምርጫ የመረጃ ማዕከል ባለሙያዎች  የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርት በደረሳቸው ወቅትም በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ማጣራት እና ምርመራ አድርገዋል። ከዚህ በታች የአሳሳቢ ኹነት ሪፖርቶች ዝርዝር ቀርቧል፡-

### 1. በተከለከሉ ቦታዎች ላይ የተቋቋመ የምርጫ ጣቢያ

**አፋ ወረዳ ገሱባ 01 ቀበሌ 07 ምርጫ ጣቢያ** የምርጫ ሕጉ ከሚፈቅደው በተቃራኒው በሕክምና መስጫ ተቋም (ጤና ኬላ) ውስጥ ተቋቁሟል።

### 2. እንዳይመዘገቡና ድምጽ እንዳይሰጡ የተከለከሉ መራጮች

**ዳሞት ጋሌ ወረዳ፣ ቡጌ ቀበሌ ቡጌ 'ሀ' ምርጫ ጣብያ** 20 ወንድ እና 9 ሴት በአጠቃላይ 29 ለመምረጥ ወደጣቢያዎች ያቀኑ ዜጎች እንዳይመርጡ ተከልክለዋል። እነዚህ ሁኔታዎች በመጀመሪያ ደረጃ መራጮቹ ይዘው የተገኙት መታወቂያ የተሰጠበት ቀን ስድስት ወር ያልሞላው በመሆኑ እንዲሁም እነዚህን መታወቂያዎች ይዘው ወደ ጣቢያዎች የሄዱት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሚመስሉ በመሆናቸው ሳይመርጡ እንዲመለሱ ተደርገዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት ለመምረጥ ከመጡ 29 ዜጐች መካከል አንዳንዶቹ ወደ ጣቢያዎች ይዘው የመጡት መታወቂያ የተሰጠበት ቀን ከስድስት ወር በላይ እንደሆነ የሚያሳይ ማለትም በ2013 ዓ.ም እና 2014 ዓ.ም መሰጠታቸውን የሚገልፁ ቢሆንም የመታወቂያዎቹ ይዘት ሲታይ አዲስ ፎቶግራፍ እና አዲስ የእጅ ጽሁፍ የያዘ በመሆኑ ምክንያት የጣቢያው ኃላፊዎች እንደዚህ አይነት መታወቂያዎች ይዘው የመጡ መራጮችን እንዳይመርጡ ከልክለዋቸዋል።

**አኮቶ ሴሬ ምርጫ ጣቢያ ቦሮዳ ዎቻ** 22 የሚሆኑ ለመምረጥ የመጡ ዜጐች መታወቂያዎቻቸው የተሰጡባቸው ግዜ በግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. በመሆኑ እንዳይመርጡ ተከልክለዋል። ከእነዚህም ውስጥ በአንዳንዶቹ መታወቂያዎች ላይ የሰፈረው የትውልድ ቀን ከድምጽ መስጫው ቀን (ሰኔ 12) ጋር ሲቀናነስ 18 ዓመት ያልሞላቸው ሆኖ በመገኘቱ ድምፅ እንዳይሰጡ ተደርጓል።

### 3. ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት

**ቡዲቲ፣ ጨጫ 'ለ' ምርጫ ጣብያ** የቀበሌ ሰራተኛ መሆኗ የተገለፀ አንዲት ሴት መታወቂያ ያልያዙ 3 ወጣት ወንዶችን አስከትላ ወደ ምርጫ ጣብያው ውስጥ በመግባት እራሷን እና ሶስቱን ወጣት ወንዶች መምረጥ አለብን በማለት ጫና ለመፍጠር ሞክራ ነበር።

አንድ ያልተፈቀደለት (በኋላ በጣቢያው በተሰማራ ታዛቢ በተደረገ ማጣራት የማዘጋጃ ቤት ሰራተኛ ነው የተባለ) ግለሰብ በተደጋጋሚ ምርጫ ጣብያ ውስጥ በመግባት ያልተገባ ጫና ለመፍጠር ሲሞክር ነበር። ይህ ግለሰብ ወደጣቢያው በመግባት የኅብረቱን ታዛቢ '*ሌላ ቦታ አልሰማህም እንዴ? ውጤቱ እኮ ይታወቃል፣ እናንተ መራጮችን እየመለሳችሁ ነው። ብዙ መራጭ ተመልሷል፣ አስመርጧቸው!!!*' በማለት ጫና ለመፍጠር ሞክሯል። የምርጫ አስፈፃሚዎቹም ምንም አይነት ግለሰቡን ከጣቢያ የማስወጣት ሙከራ አላደረጉም።

በዚሁ ጣብያ አንድ ወጣት በቀበሌ ሰራተኞች እና በምርጫ አስፈጻሚዎች መካከል ተፈጥሮ የነበረ አለመግባባትን ተጠቅሞ ረብሻ ለመፍጠር ሞክሮ ነበር። በአካባቢው ምንም የጸጥታ አካላት ካለመኖራቸውም በላይ፣ ተደውሎላቸው ሲመጡም ለአስፈፃሚዎች ጥሩ ምላሽ እንዳልሰጡ የኅብረቱ ታዛቢ ሪፖርት አድርጓል።

### 4. የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደት መቋረጥን በተመለከተ

**ቦሎሶ ሶሬ ወረዳ፣ ወርሙማ ቀበሌ፣ ቤታሎ 'ሀ' 7 ምርጫ ጣብያ** ላይ መታወቂያ ካወጡ ስድስት ወር ያልሞላቸው ድምጽ ለመስጠት የመጡ ዜጎች እንዳይመርጡ በመከልከሉ ለተወሰነ ደቂቃ የምርጫ ሂደቱ ተቋርጦ ነበር።

**ኪንዶ ኮይሻ ወረዳ፣ ቱልቻ ቀበሌ፣ 'ሀ' 2 ምርጫ ጣብያ** ላይ በሰልፍ ላይ ለነበሩ መራጮች የዝናብ እና የፀሀይ መከላከያ ባለመኖሩ ዝናብ በዘነበበት ወቅት መተረማመስ በመፈጠሩ የምርጫ ሂደቱ ለ40 ደቂቃ ያህል ተቋርጧል።

## 5. የቁሳቁሶች አለመሟላት

**በዳሞት ጋሌ ወረዳ፣ ቡጌ ቀበሌ ቡጌ 'ሀ' ምርጫ ጣቢያ** የቅሬታ መቀበያ ቅጽ እንዳልነበር የኅብረቱ ታዛቢ ሪፖርት አድርጓል።

# ረ) የኅብረት ለምርጫ የትዝብት መደምደሚያዎች እና ምክረ ሃሳቦች

## መደምደሚያዎች

የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ በወላይታ ዞን ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም የተካሄደውን የድጋሚ ህዝበ ውሳኔ የምዝገባና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶችን 117 ተቀማጭ እና 28 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን በማሰማራት ታዝቧል። በዚህ የትዝብት ክንውን ወቅትም ኅብረቱ በአጠቃላይ ሂደቱ ላይ የታዩ አበረታች መሻሻሎችን ታዝቧል።

ታዩትከታዩት መሻሻሎች ም ምርጫ ቦርድ ለዳግም ህዝበ ውሳኔው ያደረገው ቅድመ ዝግጅት፣ ሂደቱ የምርጫ ህጉን በተከተለ መልኩ መከናወኑ እና ሂደቱ በሰላማዊ ሁኔታ እንዲካሄድ አስቻይ ምህዳር መፍጠር ጥቂቶቹ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ኅብረቱ የሚከተሉትን ጠንካራ ጎኖች ታዝቧል፦

1. ቦርዱ ከፀጥታ ማስከበር እና የምርጫ ቁሳቁስ ስርጭት አንፃር ያደረገው ዝግጅት አመርቂ መሆኑ፣ እንዲሁም አብዛኛዎቹን የምርጫ አስፈፃሚዎች ከወላይታ ዞን ውጪ መመልመሉ በአዎንታዊነት ይታያል፤
2. ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከሞላ ጐደል በሁሉም ጣቢያዎች 5 የምርጫ አስፈፃሚዎች መገኘታቸው በጠንካራ ጎን ይታያል፤
3. ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከሞላ ጐደል በሁሉም ጣቢያዎች የህዝበ ውሳኔው ሂደት በምርጫ ሕጉ በተደነገገው የጊዜ ገደብ መሰረት መጀመሩ፤ እንዲሁም በሰልፍ ላይ የሚገኙ መራጮች ድምፅ መስጠት እንዲችሉ የምርጫ ቦርድ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን እስከ ምሽቱ 1:00 ሰዓት ድረስ እንዲራዘም ማድረጉ ኅብረት ለምርጫ የታዘባቸው ሌላው ጠንካራ ጎን ነው።

## ምክረ ሃሳቦች

በዚህ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት የተዘረዘሩ ጠንካራ ጐኖች እንደተጠበቁ ሆኖ ኅብረት ለምርጫ ቦርዱ ሊመለከታቸው ይገባል ያላቸውን አንዳንድ ክፍተቶች ለመሙላት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምክረ ሃሳቦች ያቀርባል:-

የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥን በአንድ ጊዜ ከማካሄድ ጋር የተያያዙ እና ማንነትን የማረጋገጥ ችግሮች ማለትም ከተሰጡ ስድስት (6) ወራት ያልሞላቸው የመታወቂያ ካርዶች እና ያለዕድሜያቸው ድምጽ የሚሰጡ ሰዎች በወላይታ ዞን በተካሄደው ድጋሚ ህዝበ ውሳኔ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው። ይህ ክስተት ቁጥሩ እየጨመረ በመምጣቱ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 18 (1) (ሐ) አንድ ሰው "*ቢያንስ ስድስት (6) ወር በምርጫ ክልሉ ውስጥ ከኖረች*" በመራጭነት ለመመዝገብ እንደሚችል/እንደምትችል የሚደነግገውን አንቀጽ መሠረት በማድረግ ሕዝበ ውሳኔው ከተካሄደበት ቀን በፊት በነበሩት ስድስት ወራት ወዲህ የተሰጠ መታወቂያ ካርድ የያዙ መራጮች ድምጽ እንዳይሰጡ የሚከለክል መመሪያ ለምርጫ አስፈፃሚዎች እንዲያወጣ አስገድዶታል።

ይህ ክስተት ኅብረት ለምርጫ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በአንዳንዶቹ የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ለአጭር ጊዜም ቢሆን መቋረጥን አስከትሏል። ከተሰጡ ስድስት ወራት ያልሞላቸው መታወቂያዎችን የያዙ መራጮች ሳይመርጡ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ አንዳንዶች የአዋጅ ቁጥር 11622/19 አንቀጽ 21(4)ን "*በሶስት ሰዎች ምስክርነት*" የሚለውን ድንጋጌ መሰረት አድርገው እርስ በእርስ እየተመሰካከሩ ተመዝግበው ድምጽ ሰጥተዋል። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎችም እንዳይመዘገቡ የተከለከሉ አንዳንድ ሰዎች አንዳቸው ለሌላቸው ምስክሮች በመሆን ተመዝግበው ድምጽ መስጠታቸውን አረጋግጠዋል። ኅብረት ለምርጫ የምርጫ ቦርድ ህጉን ለማስከበር እና በዚህም የምርጫ ማጭበርበርን ለመከላከል እያደረገ ያለውን ጥረት እያደነቀ አጥፊዎች በቀላሉ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት የህግ ክፍተት አሁንም መኖሩን ለመግለፅ ይወዳል።

## 1. የመራጮችን ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደት በተመሳሳይ ቀን መከናወናቸውን በተመለከተ

በምርጫ ሕጉ መሰረት የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ተለያይተው መከናወን ሲገባቸው በአንድ ቀን መፈጸማቸው የመራጮች የመምረጥ ሕገ-መንግስታዊ መብት የሚያጣብብ ሆኖ ኅብረቱ አግኝቶታል። እንዲህ አይነቱ ክስተት እንዳይደገም ኅብረቱ ያሳስባል።

## 2. ከቀበሌ መታወቂያ ካርዶች ጋር በተያያዘ

- ምርጫ ቦርድ መታወቂያዎችን ለማጣራት እና ህጋዊ ሰነዶችን ከህሰተኛ ሰነዶች ለመለየት በቂ ጊዜ እንዲያገኝ በተቻለ መጠን የመራጮች ምዝገባ ከድምጽ መስጫ ቀን መለየት ይኖርበታል፤
- የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ በአንድ ጊዜ በሚካሄድበት ወቅት እንዲሁም በህጉ በተደነገገው የመራጮች ምዝገባ ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ምርጫ ቦርድ ለምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት "በሶስት ግለሰቦች ምስክርነት" መራጮች እንዲመዘገቡ የሚፈቅደውን የአዋጅ ቁጥር 1162/19 አንቀጽ 21(4) እና (5)ን ከመመሪያ 6 አንቀጽ 20(3) ጋር በጣምራ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ለምርጫ አስፈጻሚዎች ቦርዱ በአፅንኦት ማሳሰብ ይኖርበታል፤
- ከህግ በተቃራኒ የቀበሌ መታወቂያ በማውጣት ላይ የተሳተፉ ተዋናዮችን መርምሮ ለህግ ማቅረብ ያስፈልጋል፤
- ለዓመታት ሲካሄድ የቆየውን የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ አሰጣጥ ሂደት እንዲፋጠን ስራ አስፈፃሚውን አካል የማግባባት (Lobby) ስራ ምርጫ ቦርድ እንዲያከናውን ኅብረቱ ያሳስባል።

## 3. አካለ መጠን ያላደረሱ ዜጎች ድምጽ መስጠትን በተመለከተ

ምንም እንኳን የምርጫ ህጉ የመምረጥ እድሜ 18 እና ከዚያ በላይ እንዲሆን ቢደነግግም የግለሰቡን አካላዊ ቁመና በመመልከት ብቻ የሰውን ዕድሜ ለመወሰን የተሻለው መንገድ ላይሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በትዝብታቸው እንዳመለከቱት የምርጫ አስፈጻሚዎች አንዳንድ መራጮችን አካላዊ ገፅታቸው ላይ በመመርኮዝ ብቻ ድምጽ እንዳይሰጡ ከልክለዋል። የመምረጥ መብትን በአካላዊ ገጽታ ላይ በመመርኮዝ ብቻ የመወሰን አሰራር የህግ ድጋፍ የሌለው ከመሆኑም በላይ በመቀንጨር ሳቢያ ዕድሜያቸው ለአካል መጠን ያደረሱ ሰዎችን ለመራጭነት በሕግ የተደነገገውን ዕድሜ (18 ዓመት) ያላሟሉ ሊያስመስል ይችላል። በሌላ በኩል ምርጫ ቦርድም ከዕድሜ በታች የሆኑ ዜጎች በህግ ያልተሰጣቸውን መብት እንዳይጠቀሙ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ወስጥ በማስገባት ኅብረቱ የሚከተሉትን ምክረ ሃሳቦች ያቀርባል ፦

- የምርጫ አስፈፃሚዎችን በአካላዊ ገጽታ ላይ በመመስረት መራጮችን ድምጽ እንዳይሰጡ ከመከልከል የዘፈቀደ ውሳኔ የሚያስቀር አሰራር ቢዘረጋ። ይህንን ዓላማ ለማሳካት የሚረዳው አንዱ መንገድ ለአካለ መጠን ያላደረሱ መራጮች ተብለው የሚጠረጠሩ ዜጐችን ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት የልደት የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ማድረግ አንዱ ዘዴ ነው።
- ቦርዱ በመራጮች ትምህርት መርሃ ግብሩ በመራጮች እና በፖለቲከኞች ዘንድ ለአካለ መጠን ያላደረሱ ዜጎችን በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ እንዲሳተፉ ማበረታታት ስለሚያስከትለው መዘዝ ግንዛቤ መፍጠር አለበት። በዚህ ድርጊት ውስጥ የሚሳተፉ ወይም ይህንን ድርጊት የሚያበረታቱ ፖለቲከኞችን እና የፖለቲካ ተዋናዮችን አካለ መጠን ያላደረሱ ዜጎች የተሳተፉበት ምርጫ ውጤት ወደ መሰረዝ ሊያመራ እንደሚችል ማስተማር አለበት።

## 4. ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጋር በተገናኘ

ኅብረቱ በምርጫ ሕጉ የተቋቋመው የቅሬታ አሰራር ኮሚቴ በጉጉት የተሞላ (Ambitious) እና ለማሳካትም አዳጋች ነው ብሎ ያምናል። ኅብረቱ ቀደም ሲል ባወጣቸው የምርጫ ትዝበት ሪፖርቶች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን መፍታት እንደሚያስፈልግ አሳስቧል። የመደመጥ መብት የመራጮች ሕገ መንግሥታዊ መብት ስለሆነ እና ዕጩዎች ይህንን መብት ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ይህንን መድረክ መፍጠር ላልተወሰነ ጊዜ ሊራዘም እንደማይችል ለማንም ግልጽ ነው። በወላይታ ዞን በድጋሚ በተካሄደው ህዝበ ውሳኔ ኅብረቱ በታዘባቸው በአብዛኛው የምርጫ ጣቢያዎች ቅሬታ ሰሚ

ኮሚቴዎች አለመኖራቸውን ታዝቧል። ኅብረቱ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የተቋቋመው 20 በመቶ በሚሆኑት ብቻ መሆኑን ለመገንዘብ ችሏል። ከዚህም በላይ፤ የተቋቋሙት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አባላት እንዴት እንደተመረጡ እና እንደተሰየሙ፣ ቅሬታዎችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ስልጠና ስለመውሰዳቸው ምንም መረጃ የለም። ከዚህ አኳያ ኅብረት ለምርጫ የሚከተለውን ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፦

- ቦርዱ በአገሪቱ ባሉ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን በጥናት በመለየት፤ ተመሳሳይ የዕድገት፤ የማንበብ እና የመጻፍ ደረጃ ላይ የሚገኙ አገሮችን (countries with similar development stage and literacy level) መነሻ (benchmark) በማድረግ አሁን በስራ ላይ በሚገኘው የቅሬታ አሰማም ስርዓት ላይ የህግ ማሻሻያ እንዲያደርግ ኅብረቱ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል።

## 5. የሲቪል ማህበራት ተሳትፎን በተመለከተ

በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልል በሚገኙ ስድስት ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች በጥር ወር 2015 ዓ.ም. እና በሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. በወላይታ ዞን በተካሄደው የዳግም ህዝበ ውሳኔ የሲቪል ማህበራት ተሳትፎ ዝቅተኛ ነበር። ከአጠቃላይ ምርጫ ውጪ ያሉ እንደሕዝበ ውሳኔ ያሉ ሌሎች የምርጫ አይነቶች ዜጎች ቀጥተኛ የዲሞክራሲ ተሳትፎ የሚያደርጉባቸው በመሆናቸው የሲቪል ማህበራት የነቃ ተሳትፎ የማድረግ፤ ዜጎችን የማንቃት እና የምርጫ ሂደቶችን የመታዘብ ሚናቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል።

*****